# የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረሕዝብ አንድነት ንቅናቄ

ETHIOPIAN DEMOCRATIC HIBREHIZB UNITY MOVEMENT (EDHUM)

*P.O. Box 73796 * Washington D.C. 20056-3796,edhum2000@yahoo.com;www.edhum.net*


======= ======= =======

## እምነትንና ሌሎች ልዩነቶችን መሠረት ያደረጉ ቀውሶች በአስቸኳይ ይቁሙ፤ የአገዛዙን ከይሲ እርምጃዎች ነቅተን በጋራ ትግላችን እናክሽፍ!

### ከኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረሕዝብ የአንድነት ንቅናቄ የተሰጠ ልዩ መግለጫ፤

ከአንድ የግፍ አገዛዝ ሥርዓት ወደ-ሌላው አፋኝና ግፈኛ አገዛዝ በሚደረግ ቅብብሎሽ ፍዳውን እያዬ ያለው ሕዝባችን ሰሞኑን በሰሜን-አፍሪቃና በመካከለኛው-ምሥራቅ የተቀጣጠለው ፀረ-አምባ-ገነኖች ሕዝባዊ መነሳሳትና እንቅስቃሴ የሚያባንነው የአቶ መለስ ዜናዊ የሕወሓት/ኢሕአዴግ የሽብር አገዛዝ ሕዝብን ልዩ-ልዩ ሰበቦችን መሠረት ሳደረገና መዘዙ ጨርሶ ከቁጥጥር-ውጭ ሊሆን ለሚችል ትርምስ ለመዳረግ የተለመደ መሰሪያዊ ማናከሱን በአንዳንድ የአገሪቱ አካባቢዎች ሲቆሰቁስ በሃዘኔታና በቁጭት ተመልክተናል፡፡ ይኽ ከይሲ አድራጎት በሙስና የጨቀዬው የአቶ መለስ ዜናዊ አገዛዝ የሚከተላቸው ፀረ-ሕዝብና ፀረ-አገር መርኆዎችና መርኃ-እቅዶች (ፖሊሲዎች) ያንገፈገፉት የኢትዮጵያ ሕዝብ ለመሠረታዊ መብቶቹ መከበር የሚያደርገውን ትግል ወደ-ከፍተኛ ሕዝባዊ መነሣሣት እንዳያድግ ለጊዜው ለማፈንና ከወዲሁ ለመከላከልና ለማጨናጎል በስሊት የተወሰደ የአጠቃላይ እቅዶቹ አንዱ ክፍል እንደሆነ ጥርጥር የለውም፡፡ ይኽ ደግሞ ከሌላ ሣይሆን እራሱ የአገዛዙ ታሪክ የሚያረጋግጥልን ሃቅ ነው፡፡

የአራችንን ለም መሬቶች በገፍና በግፍ ለባዕዳን በሃራጅ በመቸርቸር ላይ የሚገኘውና ሕዝባችንን ከጊዜ ወደ-ጊዜ እየከፋ ለሄደ ዙሪያ-ጥምጥም ችግር በመዳረግ የአፈናና የሽብር ሥርዓቱን የዘረጋው የአቶ መለስ አገዛዝ አይቀሬውን የሕዝብ መነሣሣት ለማፈን ሰሞኑን ጣምራ ስልቶችን ይዞ ዘመቻውን ተያይዞታል፡፡ በአንድ በኩል በአገር ውስጥ ሐይማኖትን (እምነትን) እና ጎሠኝነትን መሠረት ያደረጉ ግጭቶችን በስውር በማቀነባበርና በማጫር ሕዝባችንን የማይረግብ ውጥረት ውስጥ ማስገባት፣ በሌላ በኩል በተለይም ከአገሩ-ውጭ የሚኖረውን ለአገሩ አንድነትና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እውን መሆን ያለመታከት የሚታገለውንና የልብ ውጋት የሆነበትን ኢትዮጵያዊ ኅብረተሰብ በ"ኢቬስትመንትና ትራንስፎርሜሽን" ስም "ገለፃና ውይይት" ለማድረግ በሚል ሽፋን ምላሰኛ የፖለቲካ አቀንቃኝ ተላላኪዎቹን በማሰማራት ለማወናበድና በመኻሉ የበለጠ ክፍፍል ለመፍጠር እየተሠማራ መሆኑ ይታወቃል፡፡

"ለአዲስ-አበባ የተደገሰውን አፋር ላይ አመከንኩ" ብሎ የሚሞካሽ፣ በሽዎች የሚቆጠሩ ወገኖችን "በደኅንነት" ሥራ ላይ ካሠማራ፣ ድርጅታዊ የመዋቅር ሰንሰለቱን ቀበሌ ድረስ ካወረደና መንግሥታዊ ቁጥጥሩን በአምሣ ሰዎች ደረጃ ከዘረጋ፣ ፖሊስና ታጣቂውን እንዳሻው ከሚጠቀም የአፈና አገዛዝ የስድሣ አብያተ-ክርስቲያናት መቃጠል የተሠወረና ድንገተኛ ዱብ-ዕዳ ሆኖ ሊቆጠር እንደሚችል ከቶውንም ግልጥ አይደለም፡፡ በገኸው ክፍል በኩል እንደዚኽ ዓይነት ቀውሶች ከመነሣታቸውና ፈንድተው በሕዝብ ላይ ጉዳት ከማድረሣቸው በፊት አውቆ አለመከላከል፣ አንድም ኃላፊነትን መወጣት አለመቻል ነው አለያም ሆን ተብሎ የተደረገ ከመሆን አይዘልም፡፡

ምናልባት አንዳንድ የአገዛዙ ደጋፊዎች ይኽን ክስተት መንግሥት ሆን ብሎ ያደረገው ሣይሆን በኅብረተሰቡ ውስጥ ያሉ የቆዩ ቅራኔዎች የወለዳቸው ናቸው ከማለት ወደ-ኋላ እንደማይሉ የታወቀ ነው፡፡ ሆኖም በሕዝብ ይሁንታ ሣይሆን በጥሬ ጉልበት ባሰፈነው አፈና ሥልጣን ላይ ቁጢጥ ያለ አገዛዝ ስለሆነና ሕዝብን በጥርጣሬና በክፉ ዓይን የሚመለከት፣ ለሕዝብ አመኔታና ከበሬታ ግድ የሌለው በመሆኑ ሕዝብን ለማፈንና ዕለታዊ እንቅስቃሴውን ለመቆጣጠር በአገሪቱ ታሪክ ታይቶ-ተሰምቶ በማይታወቅ መንገድ በሁሉም ተቋማትና መንደርና ጎጥ ድረስ (በአንዳንድ አካቢዎች ደግሞ ከዚያም በወረደ ደረጃ) ዘልቆ የዘረጋቸው መንግሥታዊና ድርጅታዊ የስለላና የአፈና መዋቅሮቹ ይኽን መሰሉን ጥፋት ሲታቀደም ሆነ በተግባር ሲፈጸም አያውቅም ወይም ከደሙ-ንፁህ ነው ብሎ መገመቱ፣ አልፎም ለጥፋቱ ጣትን ወደ እምነቶች ለመጠቆም መሞከር አንድም አገዛዙ የሥልጣን ዕድሜውን ለማራዘም ምንም ከማድረግ የማይመለስና በቋሚነት የሚከተለውን ሕዝብን የመከፋፈል ዘይቤና ስልት ካለማጤንና በዚኽ የቆየ ታሪኩን ከመዘንጋት፣ አለያም የገባንበትን አጠቃላይ ብኸታና ለአለው አደገኛ ሁኔታ የምናሣየውን የመዘናጋት ጥንውት የሚያመላክትና የሚያረጋግጥ ከመሆን አያልፍም፡፡

ድርጅታችን የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረሕዝብ የአንድነት ንቅናቄ (ኢዴኅአን) በአገራችን ፍትኅና እኩልነት እንዲሰፍኑና አገራዊ አንድነታችን እንዲከበር የሚታገል እንደመሆኑ ሁሉ፣ የእምነት ነፃነት እንዲከበር፣ እምነቶችም ፖለቲካዊ ይዘት እንዳይኖራቸውና መንግሥትም ይሁን ማንኛውም ክፍል በፖለቲካ መሣሪያነት መጠቀሚያ እንዳያደርጋቸው አጥብቆ ይከራከራል። የአቶ መለስ አገዛዝ በተለይም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋኅዶ ቤተ-ክርስቲያን ውስጥ ሲያሻው ዓይን ባወጣ መልኩ ጣልቃ ከመግባትና እንደፈለገው በፈለገው መልክ ማተራመስ መቀጠሉን፣ አልፎም የኢትዮጵያ ሕዝብ ሐይማኖትን መሠረት ላደረገ ትርምስ እንዲዳረግ የሚያደርገውን ኋላ-ቀር ከፋፋይ ይዞታ አጥብቀን እየኮነንን፣ በቅርቡ በጅማ አካባቢ ለተደረገው ሐይማኖትን መሠረት ያደረገ መዘዘኛ የግፍ እርምጃ ተጠያቂዎች እንዲታወቁ፣ ይኸ ዓይነት አደገኛ አካሄድ በሌሎች ቦታዎችም እንዳይደገም አስፈላጊው ሁሉ እንዲደረግ፣ ችግሩ በተነሣበት አካባቢም ጉዳዩን ለዝንታለም አብሮ የኖረው የየአካባቢው ሕዝብ በመሰለው መክሮ መፍትኄ እንዲሰጥበት እንዲደረግ አጥብቀን እንጠይቃለን። ከሁሉም ከሁሉም ሕዝባችን በመንግሥትም ይሁን በአንዳንድ ቡድኖች ቆስቋሽነት እምነትን ይሁን ጎሣን መሠረት ላደረገ ሕዝብን ከሕዝብ ደም ከሚያፋስስና የመበቃቀል አዙሪትን ከሚጋብዝ መዘዙ ከበዛ ውዝግብና ቀውስ ውስጥ እንዳይወድቅ የአገር ሽማግሌዎች ያሉባቸው የጋራ አካሎችን (ኮሚቴዎችን) እራሱ ሕዝቡ በማቋቋም የሚከሰቱ ችግሮችንና አለመግባባቶችን በምክክርና በውይይት በመፍታት በተለመደው ጨዋነቱና አርቆ-አስተዋይነቱ መቻቻል፣ መከባበርና መተሣሰብ እንዳይደፈርስ ጥረት እንዲደረግ የአክብሮት ጥሪያችንን በቀጥታ ለሕዝባችን እናቀባለን።

የአቶ መለስ አገዛዝ ገና ቀደም-ሲል ጀምሮ ከፖለቲካ ድርጅቶች አንስቶ በውጭ የሚገኘውን ኅብረተሰብ ጆሮ ሊስቡና ሊያስተባብሩ ይችላሉ የተባሉ እንደ ኪነትና ስፖርት ክፍሎች የመሣሰሉትን በየተራ ለመያዝ፣ ቢያንስ ውስጣቸውን ለመቦርቦር ያላሰለሰ ጥረት ማድረጉ ይታወቃል። የእምነት ቤቶችም የዚኸ እኩይ ተግባር ሰለባ ከመሆን አላመለጡም። ከአገር-ውጭ ከሚገኘው ኅብረተሰብ የሚደርስበትን ተቃውሞ ለማብረድና አልፎም ለመቆጣጠር የሚያስችል እቅዱን በተለይም ድኅረ-ምርጫ ዘጠና-ሰባት ባወጣው ዝርዝር የውስጥ መመሪያው ግልጥ ማድረጉ ይታወሣል። ያንን በተግባር ማዋል ከጀመረ ደግሞ ውሎ አድሯል። ከዚኸም ውስጥ ስደተኛው ኅብረተሰብ በራሱ ጥረትና ወጭ በሠራቸውና ከአገዛዙ ቁጥጥር ውጭ በመሆን የሚገለገልባቸውን የእምነት ቤቶች በተለይም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋኅዶ ቤተ-ክርስቲያን ውስጥ ሰርጎ-ገቦችና ተላሎችን በማሰማራት አለመግባባቶች እንዲከሰቱና አንድነት እንዲደፈርስ ለማድረግ ጥረት ማድረጉ የአደባባይ ምሥጢር ነው። ይኸንንም ከይሲ እርምጃ ለማጠናከር ውሉ መያዣ መጨበጫ በሌለው የተውተፈተፈ እርቅ ስም ጠንካራ ገለልተኛ አቋም ያላቸውን ቤተ-ክርስቲያናት ሣይቀር ለመቦርቦር ተሞክሯል። አንዳንድ ወገኖችም የዚኸ ዋነኛ ዓላማው የኢትዮጵያውያንን አንድነት ማደፍረስ የሆነ እኩይ ሴራ ሰለባ መሆናቸው ይታወቃል።

ሙሉ በሙሉ እቆጣጠረዋለሁ ብሎ በሚፎክርበት አገር ውስጥ ያሉ ቤተ-እምነቶች ላይ የሚደርስን አደጋ ማስወገድ ያልቻለ ወይም ያልፈለገ አገዛዝስ የእርሱን እገዛም ሆነ እርዳታ ከማይፈልጉና አገልግሎቶቻቸውን በሰላም ሲሰጡ ከቆዩ ከአገር-ውጭ በሚገኙ አብያተ-ክርስቲያናት ውስጥስ ምን ጥልቅ ያደርገዋል? ቤተ-ክርስቲያናቱን እንዲያገለግሉ የተመደቡ ቀሳውስት እና አካላትስ (የቦርድ አባላት) ምን ጥንውት ቢገጥማቸው ነው በአገር ውስጥ ለሚሆነው ኃላፊነቱን መወጣት ከማይችል ከዚኸ አገዛዝስ ምንስ በጎ ነገር ጠብቀው ነው ለዚኸ መሰሪ ተልዕኮ እራሣቸውን አመቻችተው መገኘታቸው? እንደ እውነቱ ከሆነ በአገር-ውስጥ አንዱን እምነት ከሌላው እያጋጨና ደም እያፋሰሰ የሚገኝ ገዥ ቡድን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ስደተኛው ኅብረተሰብ ጥሮ-ግሮ ከሚያገኘው እየቀነሰ እምነቱንና ባህሉን ለማቆየት በሠራቸውና ደስታውንም ሆነ አዘኑን በሚያይባቸው የእምነት ቤቶች ውስጥ የሚያገባው ምንም ጉዳይ አይኖርም። ማንኛውም እምነት ሃቅንና ፍቅርን መስበክ፣ በሰዎች ላይ የሚደርስን ግፍ፣ በደልና ስቃይን ማውገዝ ያለና የሚጠበቅ ነው። የእምነት ቤቶች ከሃቅ፣ ከፍቅርና ከእውነት ውጭ የሚያሣዩት የተለዩ ቡድናዊ ወገናዊነት ሊኖር እንደማይገባ ይታወቃል። አንዳንዶች በአገዛዙም ይሁን በአንዳንድ ከፋፋይ ቡድኖች አማካይነት በሕዝባችን ላይ የሚደርሱትን ግፍና በደል ማንሣትን "ከሐይማኖታዊ እምነት ውጭ የሆነ ፖለቲካ" አድርገው እንደሚያዩት ይታወቃል። ያ ሲያስገርም ይባስ ተብሎ የአገዛዙ መፈንጫና የተልዕኮው መድረክ ለማድረግ ሽር-ጉድ ሲሉ ስናይ ግን አባባላቸው ከእምነት ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌለው ግልጥ ያደርጋል።

ለውጥ-ፈላጊው አገር-ወዳድና ዴሞክራት ክፍል አንድነቱን አጥቶና ትግሉን ቅጥ-ባጣ መልኩ ወደ-ውስጡ ማዞሩና አቅጣጫውን መሣቱ የአገዛዙ መሰሪ እቅዶች ሰምመው ለመዝለቅ አመቺ ሁኔታን መፍጠሩ አሌ የሚባል አይደለም። ለዚኸም ድኅረ-ምርጫ ዘጠና-ሰባት አገዛዙ "አዛኝ ቅቤ አንጓች" በመሆን ኢትዮጵያውያን 'መሬት እንደሚሰጣቸው' እና 'ቤት እንዲሠሩ፣ እንዲነግዱ፣ ወዘተ.' ሁኔታውን "መንግሥት አመቻችቷል" በማለት የዜጎችን የመብት ትግል በአላፊ ቁሣዊ

ጥቅማ-ጥቅሞች እንዲለውጡ ለመደለል በተደረገው ሙከራ በርካታ ወገኖችን ለማሳሳት ሞክሯል:: አከታትሎም ከአገር-ውጭ የሚኖርና በአገር-ውስጥ ቤት ያለው ሁሉ በአዲስ ምዝገባ አሻራ እንዲሰጥ፣ ባለቤትነቱን በፊርማ እያዲያረጋግጥ፣ ወዘተ በሚል ገንዘብ መሰብሰቢያ ዘዴ ብቻ ሣይሆን በዋናነት ኢትዮጵያውያንን ለመቆጣጠርና ሃብትን የድጋፍ መግዣ፣ ማስፈራሪያና መያዣ ለማድረግ ኀሊና-ቢስ ጥረት ማድረጉ ይታወቃል:: በዚኽ ዜጎችን በጥቅም ተገዢነት በእጅጉ ዝቅ-አድርጎ በገመተ እርምጃም በመደፋፈር ኢትዮጵያውያን መኻል አለመተማመንና አለመግባባት እንዲሰፍን የመሰርጀት ሥራውን በተቋማት ውስጥ ሣይቀር ይበልጥ እንዲገፋበት አስችሎታል:: ዓላማው ተቃውሞን ለማብረድ ቢቻል ለማጥፋት እንጂ ኢትዮጵያውያንን ለመጥቀም እንዳልሆነ ግልጥ ነው:: የሆነ-ሆኖ ምንም እንኳ በወያነ/ኢሕአዴጓ ኢትዮጵያ መሬት የሕዝብ/የግል ሣይሆን የገዥዎቹ በቸኛ ሃብት ተደርጎ እንደፈለጉ የሚቸረችሩት፣ እንዳሻቸው የሚሰጡትና የሚነፍጉት ቢሆንም፣ በመሠረቱ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በአገሩ ላይ ቤት ለመሥራትም ሆነ ንግድ ለመነገድ የዜግነት መብቱ እንጂ መንግሥት እንደ-ውለታ የሚሰጠውም ሆነ እያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ ለመንግሥት ደጋፊነት ውለታና ግዴታ ውስጥ የሚያስገባው ጉዳይ ሆኖ ሊቆጠር ባልተገባው::

ቀደም-ሲል እንደተጠቀሰው በውጭ የሚገኘው ኅብረተሰብ በአገራችን የአፈና አገዛዝ አክትሞ ሕዝባችን መብቶቹን የሚያስከብርበትና አንድነቱን የሚያስጠብቅበት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ባለቤት እንዲሆን የሚያደርገውን ትግልና የሚያበረክተውን አስተዋፅዖ ለመበረዝና የአገዛዙን ዕድሜ ለማራዘም "ኢንቬስትመንት እና ትራንስፎርሜሽን" የሚል ካባ ለብሶ የመጣ የመከፋፈያና የማጃጃያ ዘመቻ መጀመሩ፣ እውነት በአገር ውስጥ ሁኔታው ለሚባለው የተመቻቸ ሆኖ ሣይሆን ሁለት ተልዕኮዎችን ያነገበ እኩይ ተግባር ነው:: የመጀመሪያው ከአገሩ ውጭ የሚኖረውን ኅብረተሰብ "በመንግሥት ደጋፊና ተቃዋሚ" ለማሰለፍና ታጋዩን ሕዝብ ለመከፋፈል ሲሆን ሁለተኛው ስቃዩን እያየ ለሚገኘው ሕዝባችን "ቁርጥህን እወቀው እንኳን በአገር ውስጥ ከአገር-ውጭም ያለውን ኢትዮጵያዊ በቁጥጥሬ ሥር አድርጌአለሁ" የሚል ተስፋ-አቆራጭ መልእክት ለማስተላለፍ የሚደረግ ዘመቻ ነው:: ከዚሁ ጋር ተያይዞ ለውጭ መንግሥታትና ድርጅቶች አገዛዙ የሚከተለው አገር-አጥፊ ፖሊሲ በአገር-ውስጥ ያለው ሕዝብ ብቻ ሣይሆን ከአገር-ውጭ ያሉ ኢትዮጵያውያንም እንደሚደግፉት "በማረጋገጫነት" ለማሣየት የዘመቻው ስሊት አካል እንደሆነ መገመቱ ከባድ አይደለም:: ስለሆነም ይኽ የማጃጃያና የማዘናጊያ ዘመቻ የሚኖረውን እንደምታ ግምት ውስጥ በማስገባት ወገን ኢትዮጵያውያን በዚኽ የአገዛዙ እኩይ ወጥመድ እንዳትጠለፉ አደራችን የጠበቀ ብቻ ሣይሆን ይኽን ዘመቻ ለማክሸፍ በሚደረግ ርብርብ ሁሉም የሚችለውን እንዲያደርግና "ልማትና እድገት ያለ ነፃነትና መብት አይሆንም" የሚል የተባበረ ድምፅ በያለንበት እንድናሰማ ወገናዊ የአክብሮት ጥሪያችንን እናቀርባለን:: አገር-ወዳድና ዴሞክራት ኃይሎች መመኻላችን መኖር የሚገባውን መተከላዊ አንድነት በማጣታችን እነሆ ለአገዛዙ መሰሪ የአፍራሽ ዘመቻዎች ሁኔታውን እያመቻቸን መሆኑን ተረድተን ቢያንስ ይኽንን የሕወሓት/ኢሕአዴግ "የኢንቬስትመንት እና የትራንስፎርሜሽን" ከፋፋይ ዘመቻ ለማክሸፍ በአስቸኳይ አንድ የጋራ አስተባባሪ አካል በማቋቋም፣ በዚኽ ዙሪያ የሚንቀሣቀሱ አገር-ወዳድ ኢትዮጵያውያን ካሉም እነሱን በመደገፍና በማጠናከር፣ አፋጣኝ እንቅስቃሴ እንዲደረግ ጥሪያችንን እናቀርባለን::

ዛሬ ለሁላችንም እኩል አሣሣቢ ከሆነው የጋራ ኅልውናችን ጥያቄ አንፃር ከየራሣችን የትግል ታሪክና የአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ተነስተን የተደራጁ ኃይሎች በጠራ ግንዛቤና በአዲስ እይታ ላይ መሠረቱን ለጣለ እውነተኛና መርኅ-ተከል የትግል አንድነት ኅሊናዊም ሆነ ቁሣዊ ዝግጅት እንዲደረግ እንጠይቃለን:: የሕዝብ አንድነትን ከምንም በላይ የሚፈራው የመለስ አገዛዝ ውጥረት እየበዛ በመጣበት ቁጥር ዕድሜውን ለማራዘም ሲል እስካሁን የታዩም ሆኑ አዳዲስ ከይሲ መንገዶችን ከመጠቀምና አንዱን የሕዝብ ክፍል ከሌላው ለማናከስና ለማበጣበጥ ወደ-ኋላ እንደማይል ሊታወቅ ይገባል:: ስለሆነም የኢትዮጵያ አገር-ወዳድና ዴሞክራት ወገኖች ሁሉ አለመተባበራቸው ያስከተለውን መዘዝ አጢነው እንደ-ዋዛ ከእጃቸው ያመለጠውን አንድነታቸውን መልሰው እንዲይዙና የጋራ ኅልውናችን ግልጥ አደጋ ላይ ሆኖ ስለ-ተናጠል ድርጅት የምንጨነቅበትና የምንብሰለሰልበት ጊዜ ስላልሆነ፣ ለሕዝባችን አለኝታ የሚሆን እንቅስቃሴ እንዲደረግ ፊታችንን የምር ወደ-አንድነት እንድናዞር አደራችን የጠበቀ ነው:: በዚኽ ረገድ ድርጅታችን ኢዴኅአን ሕዝባዊ ትግላችንን ለውጤት ለማብቃት መፈጠር ስላለበት የአገር-ወዳድና የዴሞክራሲያዊ የኃይል መሰባሰብ ላይ ያለንን አቋምና አስተሣሰብ በተከታይ በቅርቡ ይፋ እንደምናደርግ በትህትና እናስታውቃለን::

አንድነት ኃይል ነው! ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!
የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረሕዝብ የአንድነት ንቅናቄ (ኢዴኅአን)
መጋቢት ፲፮ ቀን ፪ ሺህ ፫ ዓ/ም (March 25, 2011)